# የሙዋዕለ ህፃናት ዝግጅት፡-
## ወላጆች ማድረግ የሚችሉት

MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

### ንግግር ቋንቋ እና ቃላት



- ስለ እለታዊ ተግባሮችና ክንውኖች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ከልጅዎ ጋር ሆነው መፃህፍት ያንብቡ እናም ስለ ታሪክ ወይም መረጃ ተነጋገሩ።
- ለልጅዎ ጥያቄዎች ያቅርቡ።
- ለልጅዎ ጥያቄዎች መልስ ይስጡ።
- ልጅዎ በአረፍተነገሮች እንዲናገር/እንድትናገር አበረታቱ።
- ልጅዎ ከሌሎች ልጆች ጋ እንዲጫወት/እንድትጫወትና እንዲነጋገር/እንድትነጋገር ያበረታቱ።
- ነገሮች እንዴት እንደሚመሳሰሉ፣ እንደሚሸቱ፣ እና ምን ስሜት እንደሚያስተላልፉ መወያየት።
- ልጅዎ አዳዲስ ነገሮችን እንዲያደርግ/እንድታደርግና እንዲያይ/እንድታይ እድል ይስጡ። ጎረቤት አካባቢ በእግር መሄድ/Go for walks፣መንሸራሸር፣የዱር እንስሳት የሚገኙበት ክልል መጎብኘት፣ቤተመጻሕፍት/ላይብራሪ፣እና ሌሎች ፍላጎት ያላቸውን ቦታዎች።
- ስእል ለመሳል፣ለመጨፈር/ለመደነስ ሙዚቃ ለመስማት፣እና ሙዚቃ ለመጫወት ለልጅዎ እድል ይስጡ፣ተነጋገሩበት።
- ልጅዎ እየሠራ/እየሠራች ልምድ የሚያገኝበትን/የምታገኝበትን እድሎች ማመቻቸት/መስጠት ለምሳሌ፡-አንዳንድ ነገሮችን በመነካካት፣ ለማዳ የቤት እንስሳትን፣ ነፍሳትን፣ ምግብ በሚያበስሉበት ጊዜ እንዲያግዝ/እንድታግዝ ማድረግ፣ ምግቦችን በማሽተት ጣዕም እንዲለይ/እንድትለይ ማድረግ፣ ትናንሽ መኪናዎች እና የጭነት ተሽከርካሪዎችን እንዲመለከቱ ማድረግ።
- ልጅዎን ቀላል መመሪያዎችን እንዲከተል/እንድትከተል ይጠይቁ፣ልጅዎ ብዙ ነገሮችን የሚችለውን/የምትችለውን ያህል ራሱን ችሎ/ራስዋን ችላ እንዲሠራ/እንድትሠራ ያደፋፍሩ፥ለምሳሌ፡- ልብስ መልበስ፥ ጠረጴዛ ማስተካከል፥ ወይም ቁርስ ማዘጋጀት።

### ስለ ህትመት ፅንሰ ሀሳቦች




ከልጅዎ ጋር ሲያነቡ፡-

- በሽፋኑ ገጽ ላይ ያለውን ርእስ እያመለከቱ ያንብቡት።
- ሽፋኑ ላይ ስላለው ስእል ተነጋገሩ።
- ታሪኩ ወደሚጀምርበት ያመልክቱ በኋላም የት እንደሚያልቅ።
- ልጅዎ ገጹን በመገልበጥ እንዲረዳ/እንድትረዳ ያድርጉ
- አዲስ ገጽ ለማንበብ ሲጀምሩ፣ታሪኩ ከየትኛው ቦታ እንደሚቀጥል ያመልክቱ/ያሳዩ።
- ጣትዎን ከቃላቶቹ በታች በማንቀሳቀስ ቃሎቶችን ይከተሏቸው።
- እርስዎ እያነበቡ ልጅዎ በቃላቶቹ ሥር እየተከታተለች/እየተከታተለ ከሥር ጣቱን/ጣቷን እንዲያንቀሳቅስ/እንድታንቀሳቅስ ያደፋፍሩ።

### የንግግርን ድምፅ በንቃት መከታተል

- ምት የሚጠብቁ/ቤት የሚመቱ መዝሙሮችን
- ከልጅዎ ጋር አብራችሁ ዘምሩ።
- የህፃናት ግጥሞች አንብበው ከልጅዎ ጋር በቃል ይድገሙት። ሲያነቡ፣ ከሚገጥም ቃል በፊት ቆም በማለት ልጅዎ ክፍተቱን እንዲሞላ/እንድትሞላ ያበረታቱ። ለምሳሌ፡- Humpty Dumpty sat on a wall. Humpty Dumpty had a great
- በቤትዎ ዙርያ በሚታዩ ነገሮች ላይ በማመልከት ስማቸውን ይጥሩ። ለምሳሌ፡- ኳስ ከዚያ ልጅዎን ቤት የሚመታ/የሚገጥም ቃል እንዲናገር/እንድትናገር ይጠይቁ ለምሳሌ፡- tall, call, fall, wall...../ረዥም፣ መጥራት፣ መውደቅ፣ ግድግዳ/
- cat፣ dog፣ እና sat የመሳሰሉ ሶስት ቃላትን ይናገሩና የትኞቹ ቃሎች እንደሚገጥሙ ልጅዎን ይጠይቁ(ቋ)ት።
- ከልጅዎ ጋር ትርጉም-የለሽ ምልልስ መለማመጃ ይናገሩ። ለምሳሌ፡- Peter Piper picked a peck of pickled peppers.
- ልጅዎ በተመሳሳይ ድምፅ በሚጀምሩ በርካታ ቃላት ትርጉም-የለሽ አረፍተነገሮችን ፈጥሮ እንዲናገር አግዙት። ለምሳሌ፡- Betty bought a big, blue balloon.

## የሆሄይ/የፊደል ግንዛቤ




- Alphabet Song (የፊደል መዝሙር)ን ከልጅዎ ጋር አብረው ይዘምሩ።
- ልጅዎ ከአጠገብዎ ተቀምጦ/ተቀምጣ፣ የልጅዎን ስም በወረቀት ላይ ይፃፉና የጻፏቸውን ፊደላት ስም አንድ በአንድ ይጥሩ።
- ልጅዎ ስሙን/ስሟን እንዲጠራ/እንድትጠራ እና እንዲጽፍ/እንድትጽፍ ይርዱ በመጀመሪያ ልጅዎ ጥቂት ፊደላትን ብቻ ሊጠቀም/ልትጠቀም ይችል/ትችል ይሆናል ለምሳሌ፡- Jenny ተብሎ መፃፍ ያለበትን ስም JNY በማለት ይጽፍ/ትጽፍ ይሆናል።
- ከልጅዎ ጋር በመሆን፣ ለልጅዎ ክፍል ምልክት አድርጉበት።
- በማስታወቂያዎች፣ በምግብ እቃዎች ለምሳሌ cereal boxes፣ የምግብ ዝርዝር የተጻፈባቸው ነገሮች፣እና በመጽሔቶች ላይ ያሉትን የእያንዳንዱን ፊደል ስም እያመለከቱ/እያሳዩ በስም ለይተው ይጥሩ፣
- ለልጅዎ የABC መፃህፍት አንብቡ።
- ለልጅዎ ከአንድ መፅሄት አንድ ገፅ ይስጡ። በገጹ ላይ ያለውን ፊደል ያክብቡት እና ልጅዎ ተመሣሣይነት ያላቸውን ፊደላት እንዲያከብ/እንድታከብ ያድርጉ

## የቃል ግንዛቤ

- ከልጅዎ ጋር ኣብረው መፃህፍት ያንብቡ የተለመዱ ቃላትንም ያመልክቱ።
  ለምሳሌ፡- the, I, go, a, and, see, like, me, you.
- ረፍሪጂሬተርዎ ላይ የፊደል ማግኔቶች ያስቀምጡ። ልጅዎ ቀላል ቃላትን እንዲሰራ/እንዲድትሰራ ያበረታቱ።
  ለምሳሌ፡- cat, dog, mom, dad.

## ድምፅ (Phonics)

- ስእሎችን ወይም እቃዎችን ይመልከቱ። ስእሉ ወይም እቃው የሚጀምርበትን ድምፅ ልጅዎ እንዲናገር/እንድትናገር ይጠይቁት/ይጠይቋት። በዚያው ድምፅ የሚጀምር ሌላ ስእል ወይም እቃ ልጅዎ እንዲያመለክት/እንድታመለክት ያድርጉ።
- አንድ ታሪክ ወይም የአፀደህፃናት የሚገጥም ቃል እያነበቡ ልጅዎ እያዳመጠ/ እያዳመጠች በተመሣሣይ ድምጽ የሚጀምሩ ቃላትን እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ። በዚሁ ዓይነት በተመሣሣይ ድምፅ የሚጀምሩ ሌሎች ቃላትን እያሰበ/እያሰበች እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ።
- በፊደል በመገልገል ግጥሚያዎች ይጫወቱ። ለምሳሌ፡- በM ፊደል የሚጀምር አንድ ነገር እሰልላለሁ።
- ሆሄያትን ብጣሽ ወረቀት ላይ ይፃፉ እና በአንድ የወርቀት ቦርሳ ውስጥ ያስገቡ። ልጅዎ ከከረጢት/ከቦርሳ ውስጥ ወረቅት እንዲያወጣ/እንድታወጣ እና የፊደሉን ስም እና ድምፁን ለይቶ/ለይታ እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ በመቀጠል ልጅዎ በተመሣሣይ ድምፅ የሚጀምር ቃል እንዲናገር/እንድትናገር ያድርጉ።
- ፊደላትን ከመጽሔቶች ላይ በመቁረጥ ወይም ስእሎችን በመሣል ልጅዎ የፊደል ገበታ እንዲሠራ/እንድትሠራ ይርዱ።
- ልጅዎ ስሙን/ስሟን፣ እና ታሪኮችን፣ ፊደላትን እየፃፈ/እየፃፈች እንዲጫወት/እንድትጫወት ያድርጉ። ልጅዎ የጻፈውን/የጻፈችውን እንዲያሳይ/እንድታሳይ ያድርጉ ልጅዎ ለመፃፍ ያደረገውን/ ያደረገችውን ያሣየችውን/ያሣየውን ትጋት ያድንቁለት/ያድንቁላት

MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

ህትምት በDepartment of Materials Management for the Elementary Integrated Curriculum Team
ትርጉም፡- በቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ክፍል • የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት
Language Assistance Services Unit • Office of Communications
0848.19 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 2/19 • 621

Copyright © 2019 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland

